# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 111 ሰኔ 24 ቀን 2002 ገጽ 1


**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## ዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ መጪውን ፓርላማ ክርክርና ልዩነት ያለበት ለማስመሰል እቅድ ማውጣት ጀምረዋል ተባለ

የዘረኛውና አምባገነናዊው ወያኔ ገዢ ቡድን መሪዎች ስለመጪው ፓርላማ ሁኔታ ከአሁኑ መጠበብ ጀምረዋል ተባለ።

በአንዳንድ የወያኔ ባለስልጣናት ዘንድ ፓርላማውን በቡድን ከፋፍሎ ማከራከር በሚቻልበት መንገድ ላይ ምክክር መጀመሩን ለግንቦት 7 ድምጽ የዝግጅት ክፍል የደረሰ መረጃ አሳይቷል።

ይህ መጪውን ፓርላማ “የሃሳብ በያይነቱ” የሚኖርበት እና ከወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ነፃ የሆነ ተቋም ለማስመሰል የሚደረገው ጥረት በሌላም አቅጣጫዎች እየተካሄደ ያለ ይመስላል። ከሰሞኑ አይጋ ፎረም በሚባለው የወያኔ ድረ-ገጽ ላይ የወጣ ጽሁፍ ገዢው ፓርቲ በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት አግኝቶታል የተባለውን የ99.6% ድል፤ የአጋር ፓርቲዎችን ቁጥር በመቀነስ 91.2% አድርጎ ለማሳየት ሲሞክር ተስተውሏል። የወያኔ አጋር ፓርቲዎች በገዢው ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥር ስር እንዳሉ ይታወቃል።

## የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን በኦብነግ ላይ የከፈተው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በኦጋዴን ያለውን ተቃውሞ ማጥፋት ያለመቻሉ ምልክት ነው ተባለ

የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ወይም ኦብነግ መከፈሉን እና ከተከፋዩ ቡድን ጋርም ጀርመን ላይ ስምምነት መፈራረሙን አስመልክቶ ያወጣው መግለጫ በኦጋዴን ያለው ተቃውሞ ከዚህ ቀደም እንደተናገረው ላለመጥፋቱ ሌላ ምልክት ነው ሲሉ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

ኦብነግ በበኩሉ ለተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሰጠው መግለጫ ወያኔ የሚያወራው ሃሰት እንደሆነና የድርጅቱ አቋም በፖለቲካው እና በጦሩ መስክ በተግባር መታየቱን እንደሚቀጥል ገልጿል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው አገዛዝ ከሶስት አመታት በፊት ኦብነግን አጠፋለሁ በሚል ወደ ኦጋዴን ጦሩን ልኮ የጦር ወንጀል መፈጸሙን አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች መግለፃቸው ይታወሳል። በዚህ ለረዥም ጊዜ በኦጋዴን ኢትዮጵያዉያን ላይ በተደረገ ጥቃት ቁጥራቸው የማይታወቅ ንጹሃን ዜጎች የተገደሉ ለታቀደ ረሃብ የተዳረጉ ሲሆን፤ ሴቶች መደፈራቸው እና መንደሮች መቃጠላቸው ይታወሳል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የትምህርት ሚኒስቴር የግል ትምህርት ቤቶችን የቋንቋ አጠቃቀም በሚመለከት ያወጣው ፖሊሲ ቅራኔን ፈጠረ

በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የትምህርት ሚኒስቴር የግል ትምህርት ቤቶች እንግሊዝኛን እንደ ዋና መማሪያ ቋንቋ መጠቀማቸውን እንዲያቆሙ አዲስ ፖሊሲ ማውጣቱ ቅራኔን አስነስቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ፥ የአንዳንድ ግል ትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን እና የተማሪዎች ቤተሰቦች ብዙዎች እንደጠበቁት በውሳኔው ደስተኞች አይደሉም። ዘጋቢያችንን ያናገሩ ርእሰ መምህራን፥ ከጊዜ ወደጊዜ አንድ እየሆነ በመጣ አለም ተማሪዎች በአለም አቀፍ ደረጃ መወዳደር የሚችሉ ሆነው ሊታነጹ ይገባል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል። የትምህርት ሚኒስቴር ይህንን ፖሊሲ ማውጣቱም ልጆቹን የሚበድል እና ኢ-ፍትሃዊ የሆነ ውሳኔ ነው ብለዋል።

የአንዳንድ ተማሪዎች ቤተሰቦች በበኩላቸው የወያኔ ሚኒስትሮች የራሳቸውን ልጆች አዲስ አበባ በሚገኙ ውድ አለማቀፍ ትምህርት ቤቶች በእንግሊዝኛ እና በሌሎች ቋንቋዎች እያስተማሩ፤ እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ሲጨርሱ ወደ ውጭ አገር እየላኩ፤ በነሱ ልጆች ላይ እንዲህ አይነት ውሳኔ ማስተላለፋቸው እንዳስቆጣቸው ለዘጋቢያችን ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በካናዳ ዘረኛውን አምባገነን መለስ ዜናዊን በመቃወም ኢትዮጵያውያን ሰልፍ አደረጉ

በካናዳ አገር በቶሮንቶ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የዘረኛውን አምባገነን መለስ ዜናዊን በቡድን 20 አገራት ስብሰባ ላይ መገኘት በመቃወም ሰልፍ ማካሄዳቸው ተዘገበ።

የካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ስቲቨን ሃርፐር መለስ ዜናዊን መጋበዛቸው አስቆጥቷቸው ቅዳሜ ሰኔ 19 ቀን በኦንታሪዮ ፓርላማ መቀመጫ ፊት ለፊት የተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን፤ “መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ረገጣን የሚያካሂድ አምባገነን እንደመሆኑ በቡድን ሃያ ስብሰባ ላይ ቦታ ሊኖረው አይገባም” የሚለውን መልክት ለማስተላለፍ እንደተገኙ የስብሰባው አስተብባሪዎች ሰኞ እለት ባወጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

በሰልፉ ላይ ከተለያዩ የካናዳ ክፍላተ አገራት፤ ከዩናይት ስቴትስ፤ እንዲሁም ከለንደን፣ እንግሊዝ ድረስ የመጡ ተሳታፊዎች እንደነበሩ የገለጡት አስተባባሪዎች፤ “ብርትኳን ትፈታ፤ አበራሽ በርታ ትፈታ፤ አበራ የማነአብ ይፈታ፤ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ይፈቱ!” የሚሉ እና የመሳሰሉትን መፈክሮች መሸከማቸውን ገልጸዋል።

ሰልፈኞቹ ዶፍ ዝናብ በመቋቋም፥ “ዜናዊ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ቦታ አይሰጠው” እያሉ መፈክሮቻቸውን ሲያሰሙ ተደምጠዋል...

አንድነት ለሰብአዊ መብት እና ዴሞክራሲ፤ ሶሴፐ፤ ኢህአፓ - ዴሞክራሲያዊ፤ የግንቦት 7 ንቅናቄ የድጋፍ ቡድን፤ እንዲሁም የኢትዮጵያውያን የሰብአዊ መብት ህብረት ኮሚቴ የተባሉት ድርጅቶች ሰልፉን ማስተባበራቸው ታውቋል።

## ኢትዮጵያውያን ወታደሮች በወያኔ ዘረኛነት ላይ ስሞታ እያሰሙ መሆናቸው ታወቀ

በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ጦር አንዳንድ አባላት በተቋሙ ውስጥ ስለሚካሄደው ዘረኛ አሰራር ስሞታ እያሰሙ መሆኑ ታወቀ።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ፥ ቅሬታው የተቀሰቀሰው በርካታ ወታደሮች ወደ መከላከያ ኮሌጅ ለስልጠና እንዳይገቡ ከተደረጉ በኋላ ነው። እንደ ወታደሮቹ ገለፃ ይህ ሊሆን የቻለው በዘራቸው እና በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ነው። ወታደሮቹ፥ እስካሁን ወደ ማሰልጠኛ ተቋሙ እንዲገቡ እየተፈቀደላቸው ያሉት ከትግራይ ብሔረሰብ የተውጣጡ እና ጥቂት ለገዢው ፓርቲ ታማኝ የሆኑ የሌላ ብሔረሰቦች አባላት ናቸው ይላሉ።

ወደ ማሰልጠኛው ለመግባት አስፈላጊ መስፈርቶችን ሁሉ አሟልተናል የሚሉት እነዚህ የጦሩ አባላት፤ ጠንካራ አቋም ስለሌላችሁ መግባት አትችሉም መባላቸውን ተናግረዋል። ጠንካራ አቋም ማለት ደግሞ ለገዢው ፓርቲ ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው ብለዋል።

የወያኔ አገዛዝ ከዚህ ቀደም በነበሩት አገዛዞች ስር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ፤ በተለይም በጦሩ ውስጥ መዋቅራዊ ዘረኛነትን ማስፈኑን የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ ቀደም ባወጣቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ማጋለጡ ይታወሳል። በርካታ የጦሩ አባላት ከሚደርስባቸው የዘር አድሎ በመሸሽ አገራቸውን ጥለው መሰደዳቸውም ይታወቃል።

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት በተለያዩ ከተማዎች የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን እያካሄደ ነው

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ወይም ኢሳት በተለያዩ የአለማችን ከተሞች ስኬታማ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን እያደረገ መሆኑ ታወቀ።

እስካሁን በአሜሪካን አገር በዋሽንግተን ዲሲ፣ በሲያትል እና በዳላስ፤ እንዲሁም በስዊድን አገር በስቶኮልም ከተማ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች የተደረጉ መሆናቸውን ለቴሌቪዥን ድርጅቱ ቅርብ የሆኑ ግለሰብ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል። ከሳምንት በፊት ሰኔ 12 ቀን በዳላስ ከተማ በተካሄደው ዝግጅት ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተገኝተው ድጋፋቸውን መለገሳቸውን የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ ድረ-ገጽ ላይ የወጣ ዘገባ ገልጿል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔን ከነእብሪቱ ለማስወገድ ውጤታማና ዘላቂ ትብብር እንመሥርት!

የዓለም ታላላቅ ሚዲያዎች በአንድ ድምፅ ወያኔን "አፈርንብህ" እያሉት ነው። ምዕራባዊያን በተለይም መንግሥታቱ በወያኔ ላይ የተወሰነ ተስፋ ነበራቸው። ከመለስ በርካታ ምላሶች አንዱ በዚህ ተግባር ሰልጥኗልና ለዘመናት በጮሌነት ሲያታልላቸው ኖሯል። ዘንድሮ - በ2002 ዓ.ም. በምርጫ ስም ተፈጽሞ በዓይናቸው ያዩት ነገር በጆሮዓቸው ሲሰሙት የቆየውን ፈጽሞ አይስልም።

በዚህም ምክንያት ምዕራባዊያን ሚዲያዎች በወያኔ ላይ የተሰማቸውን እፍረት በዝርዝር እየነገሩን ነው። ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ብቻ ኒዮርክ ታይምስ፣ ሬውተር፣ አሶሼትድ ፕሬስ፣ ሎስ አጀለስ ታይምስ፣ ብሉምበርግ፣ ዘ አትላንታ፣ ቪኦኤ፣ ቢቢሲ እና ሌሎች በርካታ የዜና አውታሮች በወያኔ አሳፋሪ የምርጫ ተውኔት ላይ ጽፈዋል፤ ተችተዋል። "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም" እንዲሉ ወያኔ "የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ነው ብላችሁ ተቀበሉኝ፤ አለበለዚያ ግን እናንተንም ወዮላችሁ" እያለ ይዝትባቸው ጀምሯል። የወያኔን ግብዝነት ከሚገልፁ በርካታ ነገሮች አንዱ ይኸ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ባይነቱ ነው።

ወያኔ በ97 ምርጫ ተሸንፎ በጉልበት ይዞ የቆየውን ሥልጣን በ2002 ህጋዊ ለማስመሰል የከወነው ትዕይንት የባሰውን እራቁቱን አስቀርቶት ከወዳጆቹ ጋር ሳይቀር አቀያይሞታል። እሱ ግን አሁንም ስለ ምርጫው ውጤት ትክክለኝነትና ፍትሃዊነት ማብራሪያ ካልሰጠሁ ሞቼ እገኛለሁ እያለ ነው።

አንደኛው ክርክር "99.6 በመቶ አሸነፍክ መባሌ ቀርቶ የአጋር ድርጅቶች ድርሻ ተቀንሶልኝ 91.2 በመቶ ይባልልኝ" የሚል ነው። መቼም ይኸ ክርክር ለውጭ አገር ሰዎች እንጂ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የታለመ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የአፋሩ አብዴፓ፣ የጋምቤላው ጋሕዴአን፣ የሶማሊው ሶሕዴአግ፣ የቤሻንጉል ጉሙዙ ቤጉሕዴአን እና የሀረሪው ሀብሊ በአንድ ሚዛን፤ የአማራው ብአዴን፣ የኦሮሞው ኦህዴድ እና የደቡቡ ደኢህዴን በሌላ ሚዛን አስቀምጠን ብናወዳድራቸው ሁሉም እኩል ገለባዎች መሆናቸውን እናውቃለን። ከስማቸው መብዛት በስተቀር ሁሉም እኩል የወያኔ ተላላኪዎች መሆናቸው እነሱ ራሳቸው በተደጋጋሚ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። ከአዲሱ ለገሠና አባዱላ ገመዳ፤ ከመሃመድ ድሪርና ከእስማኤል አሊ ሴሮ የቱ ለወያኔ ይቀርባል ብለን የምናወዳድርበት አንዳችም ምክንያት የለንም። ስልቻ ቀልቀሎ፤ ቀልቀሎም ስልቻ ነው እንደተባለው ሁሉም የወያኔ ምንደኞች ናቸው፤ እነሱም ይህንን አይክዱም። ሆኖም ይኸ ክርክር የምዕራባዊያንን ልብ ያለሰልስልኝ ይሆናል ብሎ ገፍቶበታል። የውስጡን ጉድ መረዳት ቢያስቸግራቸው እንኳን በእነሱ ዓይን ሲታይ በ99 እና በ91 በመቶ መካከል ያለው ለውጥ እምብዛም ነው።

ሁለተኛ የክርክር አቅጣጫ ደግሞ "ልማት አምጥቻለሁ፤ ይህ ደግሞ በራሱ ሕዝብን ቀጥቅጬ የመግዛት መብት ይሰጠኛል" የሚል ነው። ነገር ግን ጠዋት ማታ የሚለፈፍለት የኢኮኖሚ እድገት የቁጥር ጨዋታ ውጤት መሆኑ ፈረንጆቹም መጠርጠር ጀምረዋል። "የታል ምግቡ?" "የታል ሥራ?" "የታለ የጤናው አገልግሎት?" በተባለ ጊዜ ቁጥሮች አያድኑትም። ወያኔ ደግሞ ለዚህ ማምለጫ "ፈጣን ልማት ስለሚፈጥራቸው ችግሮች" አዳዲስ ግኝቶችን እያስተዋወቀ ነው። ወያኔ ፈጣን ልማት ባመጣው ችግር ምክንያት ሕዝብ ይራባል፣ ይጠማል፣ ይታረዛል፣ ይሞታል እያለ ልማት የሚባለው ነገር የሚፈራና የሚጠላ ክፉ መንፈስ እያደረገው ነው።

የወያኔ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ከሁሉም በላይ ጎልቶ የታየው ደግሞ "በድምፃችን ይከበር" ሰልፍ ላይ ነው። የመለስ ዜናዊ የቀድሞ ወዳጆች ይኸን ሰልፍ በአደባባዩ ከተሰቀለው የመለስ ዜናዊ ምስል ጋር ሲቀርብላቸው የበርሊን ግንብ ከፈረሰ ሃያ አመት በኋላ ሌላ ተመሳሳይ ግንብ አዲስ አበባ እየተገነባ እንደሆነ እንዲታዘቡ አስችሏቸዋል።

"የአፈርንብህ" እና "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ክርክሮችን ለጊዜው እዚሁ ላይ እናቁምና ወደ ራሳችን እንመለስ። መለስ በዚህ ምርጫ ግልጽ የሆነ መልዕክት ለሁላችንም አስተላልፎልናል፤ ንቀቱና እብሪቱን አሳይቶናል። ምላሻችን ምንድነው?

በግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት ምዕራባዊያን የወያኔን እኩይ ተግባራት እየተረዱ መምጣታቸው መልካም ቢሆንም ነፃነታችንን ማስከበር የምንችለው እኛው ብቻ ነን። የወያኔን እብሪት የሚመጥን የተባበረ ኃይል በአስቸኳይ መፍጠር ይኖርብናል።

አሁን የምንፈጥረው ኅብረት ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተሞከሩ ኅብረቶች መንገድ ላይ የሚቆም መሆን የለበትም። አሁን የምንፈጥረው ኅብረት ወያኔን አስወግደን በምትኩ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት እስከ ማቋቋም የሚደርስ አስተማማኝ ተቋም መሆን ይኖርበታል። እንዲህ ዓይነቱ ውጤታማና ዘላቂ የሆነ ኅብረት ለመፍጠር በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ሳይቀር በቂ ዝግጅት ሊደረግ ይገባል። እንዴት መነጋገር እንዳለብን ሳይቀር መነጋገር ይኖርብናል። ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ችሎታ፣ ሙያና ዝንባሌ ያላችሁ ወገኖቻችን በሙሉ ልባቸው ሊረባረቡበት ይገባል እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የመገናኛ ብዙሃንን ስርጭት ለማፈን በየአመቱ በሚሊየኖች የሚቆጠር ዶላር እያፈሰሰ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን ስርጭት ለማፈን በየአመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር እያፈሰሰ ነው ሲል አዲስ ነገር አንላይን የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ዘገበ።

አገዛዙ ተቃዋሚ ቡድኖች ከውጭ አገራት ወደ ኢትዮጵያ መረጃ ለማሰራጨት የሚያደርጓቸውን ሙከራዎች በቀጣዮቹ አመታት ያፋፍማሉ፤ እንዲሁም የውጭ መንግስታት እና ተቋማት ይህንን ሙከራቸውን ያግዛሉ የሚል ስጋት እንዳለበት አዲስ ነገር በገዢው ፓርቲ ዘንድ ያሉ ምንጮቹን ጠቅሶ በዘገባው ገልጿል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ወይም ኢሳት ከተመሰረተ በኋላ ይህ ስጋት በወያኔ ላይ እንደበረታ የገለጸው ዘገባ፤ በተለይም በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት የውጭ አገራት መንግስታት እና ተቋማት የወሰዷቸው አቋሞች ተቃዋሚ ቡድኖች ኢትዮጵያ የሚደርሱ መገናኛ ብዙሃንን እንዲያቋቁሙ ለመርዳት ሊነሳሱ ይችላሉ በሚል አገዛዙ ስጋት ላይ መውደቁን አስረድቷል። በዚህም ምክንያት ወያኔ ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፉ የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙሃንን ለማፈን ከፍተኛ መጠን ያለው የህዝብ ገንዘብ በማባከን ላይ መሆኑ ታውቋል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ባወጣው ርእሰ አንቀጽ የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት እያደረገ ያለውን ድጋፍ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርቦ፤ ሌሎች ወደ ኢትዮጵያ የሚሰራጩ የመረጃ አውታሮች እንዲመሰረቱም ሃሳብ አቅርቧል። ንቅናቄው፥ "መረጃ የማግኘት መብታችንን ማንም አምባገነን ሊያፍነው እንደማይችል ለመለስ ዜናዊና ለተባባሪዎቹ በመተባበር እናሳየቸው" ብሏል።

### የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን በኦብነግ ላይ የከፈተው የፕሮፓጋንዳ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዛ ሁሉ እልቂት በኋላ ኦብነግን ፈጽሞ ሰብሬያለሁ ሲል የቆየው አገዛዝ ተደጋጋሚ ጥቃት ሲደርስበትና ያንንም በተዘዋዋሪ ለማመን ሲገደድ መቆየቱን ከዚህ ቀደም ባወጣናቸው ዘገባዎች አሳይተናል።

የወያኔ ባለስልጣን የሆነው አባይ ጸሃዬ፥ ኦብነግ ባጠቃላይ 250 ወታደሮች እንደነበረው እና ተከፋዩ ቡድን የዛን ግማሽ መውሰዱን ለሬውተርስ ተናግሯል። ይህንን በሚመለከት አስተያየት የጠየቅናቸው የፖለቲካ ተንታኝ፥ "እኔ ኦብነግ ስንት ወታደሮች እንዳሉት አላውቅም። ነገር ግን እሱ እንደሚለው 250 ብቻ ይዘው በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች በአካባቢው ያሰፈረውን አገዛዝ እንዲህ ካስጨነቁት፤ ይህ የሚናገረው ስለ ወያኔ ድክመት ነው። ይህ እውነት ከሆነ በየዱሩ ለሚኳትኑት ኢትዮጵያውያን ታጋዮች ተስፋ የሚሰጥ ነው።" ብለውናል።

### በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የትምህርት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ ባለስልጣናት በየአመቱ በአስር ሺሆች የሚቆጠር ዶላር ለትምህርት ቤቶች በመክፈል ልጆቻቸውን በውጭ አገራት እንደሚያስተምሩ ይታወቃል። አንዳንዶቹ ለልጆቻቸው ጥበቃ ሳይቀር ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚከፍሉ ይነገራል። በኢትዮጵያ የአገዛዙን ባለስልጣናት ሃብት የሚመረምር መንግስታዊም ሆነ ገለልተኛ ተቋም አለመኖሩ ይታወቃል። በአንጻሩ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብር በየአመቱ ከመንግስት በጀት እንደሚጠፋ የኦዲት ሪፖርቶች ያሳዩ ሲሆን፤ ገንዘቡ የደረሰበትን ለማወቅም ገለልተኛ ምርመራ ተካሂዶ አያውቅም።

ሃይለ ሀሳብ
የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 111 ሰኔ 24 ቀን 2002 ገጽ 3

# ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ

**(ይህ መግለጫ ባለፈው ዓመት በ2001 ዓ.ም በነሐሴ ወር የወጣ ሲሆን ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያለፍንበትንን፣ የአሁኑን የወደፊቱንም በጥልቀት የዳሰሰ በመሆኑ በድጋሚ እንዲነበብ እንጋብዛለን) (ክፍል 3)**

በመጨረሻም ሕዝብ በምርጫ ለውጥ ይቻላል የሚለውን እምነት ጨርሶ ከአዕምሮው አውጥቶ በምትኩ የሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ከወያኔ በጎ ፈቃድ ጋር እንደተያያዘ ቆጥሮ በፍርሃት እንዲዋጥ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የስነልቦና ጦርነት ያለማቋረጥ ተደርጎበታል፡፡ ለማስረጃም ያህል

- የምርጫ 97 ዋና ዋና ተሳታፊ የነበሩ ወጣቶችን፤ ነጋዴዎችና የገጠር ነዋሪዎችን በእሥር፤ በስደትና በሞት ሲቀጣ ሌሎችን ደግሞ እየተጠሩ በማስፈራራት፤ በመተዳደሪያ ሥራቸውና ንግዳቸው ላይ እገዳ በማድረግ፤ ሥራን በማሳጣት፤ ያለአግባብ ግብር በመጫን ... ሁለተኛ ከተቃዋሚ ጎን እንዳይቆሙ ያስፈራራል።
- ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ሥራ ፍለጋ የሚስማራውን ተመራቂ ወጣት ሥራ ለማግኘት ወያኔን መደገፍና የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች ውስጥ አባል መሆን ግዴታ እያደረገበት ነው።
- በማንኛወም መንገድ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙንት የሚፈጥር ሰው በራሱና በቤተሰቦቹ ኑሮና ደህንነት ላይ አደጋ እንደሚፈጠር ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ይነገረዋል።

ከላይ በተዘረዘሩት እርምጃዎች አማካይነት በምርጫ 2002 አሸናፊ አድርጎ የሚያወጣውን «ተቃዋሚዎችን የማዳከም፤ የሲቪል ማኅበራትን የፖለቲካ ተሳትፎ ማጥበብንና የሕዝብንም ቅስም የመስበር የምዕራፍ አንድ ዝግጅቱን አጠናቅቂያለሁ» ብሎ አምኗል። የሁለተኛው ምዕራፍ መርሃ ግብሩን ደግሞ በቅርቡ እንደሚጀምር አንዳንድ ሁኔታዎች እያመለከቱ ነው። በዚህ በሁለተኛ ምእራፍ የሚጠበቀው ዋነኛ እርምጃም ወያኔ ለራሱ በተመቻቸ የጊዜ መስኮት ውስጥ ለምርጫ ውድድር ዝግጁ ነኝ ብሎ ማወጅና ለምርጫውም አጃቢዎችን መፈለግ ነው። ለዚህም የሚጠቀምበት ዘዴዎች የሚከተሉትን እንደሚመስሉ ይጠበቃል፤

- በአለቀ ሰዓት ለሚሳተፉ ተቃዋሚዎች የተወሰነች የሚዲያ ዕድል መስጠት፡ ይህም እድል እንደ ምርጫ 97ቱ ለፓርቲዎች የሚሰጥ ሳይሆን ለግለሰብ ተወዳዳሪዎች እንዲሆን ማድረግ፤ በዚህም ከ500 በላይ የፌደራል ፓርላማ ተወዳዳሪና በሺዎች የሚቆጠር የክልል ተወዳዳሪ በሚሰጠው 5 ደቂቃ ምንም ሳይናገር ጊዜውን እንዲጨርስ ማድረግ፤
- ከተወሰነላቸው ወንበር በላይ ለማሸነፍ ዕድሉም ሆነ የመጋፈጥ ፍላጎት ላላቸውም ለሌላቸውም ኃይሎች በመንግሥት ስም የገንዘብ ድጎማ ማድረግ፤ አሁን በቅርቡ እንደተገለጸው ደግሞ ይህንን የገንዘብ ድጎማ አስቀድሞ ወያኔ ለራሱ ፍላጎት ማስፈጸሚነት ባዘጋጀው የማጭበርበር ምርጫ ለሚሳተፉ ብቻ ማድረግ፣ ገንዘቡን ወስደው ምርጫው ነጻና ፍትሃዊ አይደለም ብለው ምርጫ አንሳተፍም የሚሉ ድርጀቶች ግን ለምርጫው የተሰጣቸውንና ለምርጫ ያጠፉትን ገንዝብ መልሰው እንዲከፍሉ የሚል ህግ ማውጣት፤ በእዚህም ምርጫን ሳይወዱ በግድ ነጻና ፍትሃዊ ሆነ አልሆነ ተገደው እንዲሳተፉ ማድርግ፤
- ይህንን ውድድር አልባ የሆነ ምርጫም ለውጪ ዓለምና ለእርዳታ ሰጭ አገሮች እንደ ዲሞክራያዊ ተግባር ለማሳዬት ይረዳ ዘንድ የውጭ ታዛቢዎችን መጋበዝ፤
- ብዙ የተማረ የሰው ሃይልና ምናልባትም በሌላው ክልል አመለካከት ላይ "ተጽእኖ" ሊያመጡ ይችላሉ ተብለው የሚታመኑ ዋና ዋና ከተሞችን፤ በተለይም አዲስ አበባን ከሌላው ክልል ምርጫ ለይቶ ምንም ለውጥ በማያመጣ ጊዜ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ፤
- በመጨረሻም እየተሰማ ያለው በዚህ በወያኔ ተውኔት ለመሳተፍም ተቃዋሚዎች የሥነ ምግባር ስምምነት ከወያኔ ጋር እንዲፈራረሙ ማድረግ ነው።

የ2002 ምርጫን በሚመለከት ወያኔ በሁለት ምዕራፎች ከፍሎ ያደረገው ዝግጅት ከላይ የዘረዘርናችውን ይመስላል። በሕዝብ ወገን ያሉ ተቃዋሚ ኃይሎች የዚህ የወያኔ ተንኮልና አፈና የመጀመሪያ ተጋፋጮች እንደመሆናቸው መጠን ይህንን ያጡታል የሚል ግምት የለንም። ከሕዝቡ አካባቢ የሚሰማው ስሜት ተቃዋሚዎች ምርጫ ውስጥ እንዲገቡ የማይፈልግ መሆኑን በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕዝብ ለነኝሁ ተቃዋሚዎች እያሰማ መሆኑን ተቃዎሚዎች ከሕዝብ ጋር በሚያደርጉዋቸው ምክክሮች እያስታወቁ ነው፡፡ ግንቦት 7 ንቅናቄ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች እራሳቸው ካሉበት ዓይነተኛ ይዞታ በመነሳት ምርጫውን አስመልክቶ አስፈላጊውን ምላሽ እንደሚሰጡ ያምናል። ሆኖም ግን የዲሞክራሲና የአገር ማዳን ትግሉ አንድና በጋራም የሚመለከተን ጉዳይ ነውና እኛም ካለንበት ሁኔታ የሚታየንን ለአገር አቀፍ ትግላችን መደረግና መወሰድ ያለበትን አቋም የመግለጽ ግዴታ አለብን ብለን እናምናለን። በዚህም መንፈስ ግንቦት7 ምርጫ 2002ን አስመልክቶ የሚከተሉትን የትግል ጥሪዎች ያደርጋል።

### የግንቦት 7 ጥሪዎች

### ጥሪ ኢትዮጵያ ህዝብ

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስና የጥቂት ተባባሪዎችን መሠሪነት በምርጫም ሆነ በሌላ ሁኔታ መንገር "ቀባሪውን እንደ ማርዳት" ይቆጠራል። ሕዝባችን የሚፈልገው ከዚህ አፋኝና አገር አጥፊ የገዢ ቡድን እንዴት መላቀቅ እንደሚችል በተግባር ታግሎ የሚያታግለው ኃይል ነው። በዚህም መሠረት ግንቦት7 የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ 2002ን አስመልክቶ የሚያስተላልፈው መልዕክት የመለስ ቡድን በሰፊ የገንዘብ ወጭ፤ በማያቋርጥ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና በመጠን የለሽ የሰው ኃይል ማሠማራት ለሚፈጥረው የማደናገሪያ ቲያትር ጆሮውን እንዳይሰጥ ነው።

ደግመን ደጋግመን ለሕዝባችን የምንለው ነፃ ምርጫ ምን እንደሚመስልና ምን ዓይነት ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ሙሉ በሙሉ ነጻ ባልነበረው በ97 ምርጫ አሳይተሃል። በተጨማሪም የወያኔ ምርጫ የራሱ የገዢው ፓርቲ ጨዋታ እንደሆነ በአለፈው የክልል ምርጫ በልዩ ልዩ መልኩ (ለምሳሌ ካርድን ከመቅደድ ጀምሮ እስከ ካርዱ ላይ ተቃውሞ እስከ መጻፍ ድረስ እንዳደረኸው) ለዓለም ሕዝብና ለራሱም ለወያኔ በማያሻማ መልኩ አሳይተሃል። ስለዚህም መጪውን የመለስን የምርጫ 2002 ጨዋታ ችላ ብለህ በሁሉ-ዓቀፍ ተሳትፎ ለዲሞክራሲና ለአገር ግንባታ የሽግግር ሥርዓት መምጣት አምርረህ ለመታገል ቆርጠህ ተነስ። ጉልበትህን፤ ንብረትህንና ቅዱስ የሆነውን መስዋዕትነትህን ነፃነት ለፍትህና አንድነት ትግል ሳትቆጥብ አብረኸን እንድትሰለፍ ጥሪ እናደርጋለን።

### ጥሪ ለሃቀኛ ተቃዋሚዎች

የመለስ-በረከት ቡድን በየደረጃው የተበተበውን የአፈናና የማደናገሪያ እርምጃ ገፈት ከእናንተ የበለጠ የቀመሰው የለም። በሕዝብ የተከበሩ መሪዎቻችሁ መታሠር ጀምሮ እስከ አባላቶቻችሁ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መዋከብና መታፈን ምን እንደሚመስል ለእናንተ አይነገርም። እንድምታውቁት ከዚህ ሁሉ የእብሪትና የብልግና ድርጊቱ በኋላ ነውር የለሹ የወያኔ ቡድን ከእናንተ ትልቅ ችሮታ ለመጠይቅ ይመጣል። ይህም ችሮታ አሸናፊነቱን አስቀድሞ ባረጋገጠበት ሰአት የምርጫ 2002 አጃቢዎቹ እንድትሆኑ የተለመዱ አማላጆቹንና የማታለያ ቡርቲውን ይዞ ይቀርባል። በዚህም መለስ ከሠለጠነው ዓለም መድረክ ላይ በወጣ ቁጥር በግልፅም ሆነ በውስጠ ታዋቂ ቋንቋ የሚቀርብለትን የምርጫ 97 ዘራፊነቱን ክስ በእናንተ አጃቢነት ሊሰርዝ ይፈልጋል።

እናንት እኮ የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎችን የምታውቁ ብቻ ሳትሆኑ የእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ደራሲዎች ናችሁ። እናንተ እኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ በተመለከተ "ብልጥ ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል" ከሚል የፖለቲካ ቀልድ እንዳለፈ የዓይን ምስክር ናችሁ። ብዙዎቻችሁ እኮ በምርጫ 97 ሕዝባችን ከድል አፋፍ በአጋዚ ጦር እየተደበደበ ወደ ታች እንዲወርድ ሲደረግ አብራችሁ ገፈቱን የቀመሳችሁ ናችሁ። ወያኔ ይህን ምርጫ ተብዬ እያዘጋጀ ያለው ዴሞክራሲያዊ ለመባል ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ ምርጫ የደረሰበትን የ97 ውርደት እናንተን ምንም ልትንቀሳቀሱ በማትችሉበት ሁኔታ በውሸት ምርጫ አዋርዶ "በዝረራ አሸነፍኩ" ብሎ ለመፎለል ነው፡፡ እነሱ እንደሆን ለራሳቸው ምንም ክብር የላቸውም፡፡ ሕዝብ የሚያከብራቸውን ወገኖች እንደነሱ ሲዋረዱ ማየት ትልቅ ደስታ የሚሰጣቸው ህመምተኞች መሆናቸውን አትርሱ፡፡ ስለዚህ በእኛ እምነት አሁን የሚያስፈልገው ለሕዝባችን፤ ለዓለሙ ማኅበረሰብና ለራሱም ለወያኔ የመለስ-በረከት ቡድን፤ እነሱ የይስሙላ ምርጫ ሲሉና ሕዝቡና የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ ነፃ ምርጫ ሲሉ ያለውን ከፀሐይና ከጨለማ ያልተናነሰ ልዩነት በድፍረት ማሳየት ነው። በዚህም እርምጃ እውነተኛ የሕዝብ ወገኖች፣ ሳይጀመር ከወዲሁ በተጨናገፈ ምርጫ ገብቶ ከመተራመስ ይልቅ፣ ለማይቀረው፣ ምርጫን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለማድርግ መደረግ ላለበት ትግል አቅማቸውን አስተባብረው ሕዝብን ማደራጀትና ማስተማር የበለጠ ጥቅም እንዳለው አውቀው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

### ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ኃይሎች ማሳወቅ ያለብን አቋም

በአገራችንና በአካባቢያችን የሚሆነው ሁሉ «የብሄራዊ ጥቅማችንን፣ ደህንነታችንንና ሌሎችንም ፍላጎቶቻችንን ይነካል» የሚሉ ዲሞክራቲክ ሀገሮች በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ሥርዓት የመለስ አፈ ጮሌነትና ተራቀቅኩ ባይነት የአንድ ሰው ተውኔት እንደሆነ ከተረዱ ሰንብተዋል። ከሰውዬው ተውኔት በታች ያለው መንግሥት የጥቂት አምባገነኖች አገዛዝ እና በሙስና ከላይ እስከታች የተዘፈቀ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ሆኖም ግን የአገሪቱን የወታደራዊ፣ የፀጥታና የኢኮኖሚ ዋና ዋና ክፍሎች በዘር ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በሌሎች የዓለም ክፍሎች እንደታየው አደገኛ የርስ በርስ ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ ብለው ስለሚፈሩ ይጠነቀቃሉ። መለስና ቡድኑን፣ የጂኖሳይድ ዎችና የሌሎችም የሰብዓዊ መብት ተሟጓቾች በከፍተኛ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በየጊዜው የሚከሷቸው ሰዎች መሆናቸውን እነዚህ መንግሥታት ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ መንግሥታት በዲሞክራሲያዊ ዓላማ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ቢቆሙ እንኳን ሕዝብን ወይም የሕዝብ መሪዎችን ተክተው ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲና ደህንነት ይታገላሉ፤ ወይም ይህንን ሥርአት ያመጣሉ ማለት አይደለም። እንዳያውም የእለት-ተእለት የሀገራቸው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

ጥቅም ብዙ ጊዜ የቆሙለትን የዴሞክራሲ እምነት በሚጻረር መልኩ ከእንደ እነመለስና-በረከት ቡድን ዓይነቶች ጋር ሲያቆማቸው ደጋግመን አይተናል። ይህ ሁኔታ ምርጫ 2002ን አስመልክቶ አንዳንድ ግንዛቤን እንድንወስድ ያስገድደናል። የውጭ ኃይሎች ምርጫ 2002ን በሚመለከት እንደ ተለመደው "በአንተም ተው አንተም ተው" አቀራረብ ተቃዋሚዎች ከወያኔ ጋር እንድንሰለፍ ይጠይቃሉ። "ደግን ልጅ እናቱ አትወደውም" እንደሚባለውም "እሺ እሺ" የምንላቸውን ክፍሎች አጥብቀው ይጫናሉ።

አሁንም እንደተለመደው በሥልጣኑ የመጣን ሁሉ ወይ ፍንክች የሚለው ወያኔ እነዚህን የውጭ ኃይሎች «እኔ በሚጠቅመኝ መንገድ ባዘጋጀሁት ምርጫ ተቃዋሚዎችን ካላመጣችሁ ብሎ እሪ» ማለቱ አይቀርም። ከዚህም አልፈው እነዚህ ኃይሎች ምርጫ በነፃነት እንዲካሄድ አጥብቀው እንገፋለን ካሉ የመለስ-በረከት ቡድን ከተወዳዳሪ ሌሎች አገሮች (ለምሳሌ ቻይና) ጋር የጠበቀ መቀራረብን እንደሚያደርግ ግልጽ ምልክቶችን እያሳዬ ነው። እንደሚታወቀው ይህንን ስናይ የመጀመሪያ ጊዜያችንም አይደለም። እነዚህ የምእራብ መንግስታት ይህም ወያኔ አካሄድ ያሰጋቸዋል፡፡

እኛ ማድረግ ያለብን፣ እኛ ለዲሞክራሲ፣ ለመልካም አስተዳደርና ኃላፊነት ላለው ሥርዓት ተገዢዎች እንደሆንን በአቋምና በተግባር አጥብቀን ማስረዳትና ማሳየት ነው። ለዚህም ዋና መለያችን አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ተወዳድረን ለማሸነፍ የሚያስችለን ምንም ገደብ የሌለብት ነፃ የምርጫ ሁኔታ ከመፍጠር በታች ምንም ድርድር ውስጥ እንደማንገባ በግልጽ ማቅረብ ይኖርብናል። እነዚህ የውጭ ሰዎች «ለምርጫው በቀረው አጭር ግዜ ውስጥ ለምታነሷቸው ትላልቅና ግዜ ወሳጅ ጥያቄዎች እንዴት ምላሽ መስጠት ይቻላል? የዛሬውን ግቡልንና ለሚቀጥለው ምርጫ ነገሮች ይስተካከላሉ፤ ዴሞክራሲ ሂደት ነው» ማለታቸው አይቀርም፡፡ መልሳችን «ይህንንማ ከዛሬ አራት አመት በፊትም ሰምተነዋል፡፡ ሁኔታዎች ሲብሱ እንጂ ሲሻሻሉ አላየንም፡፡ ዴሞክራሲ አዝጋሚ ሂደት የሚሆነው አብዛኛው ሕዝብና የፖለቲካ ልሂቁ ትርጉሙ ሳይገባው ሲቀር ነው፡፡ በአገራችን የዲሞክራሲ ትርጉም ፈጽሞ ያልገባቸውና ጣፋጭነቱ የሚመራቸው ዘረኛ በሆነ መንገድ ከገነቡት ሥልጣንና ጥቅም ይነቅናል የሚሉ ጥቂት ኋላቀር ዘረኞች ናቸው፡፡ ለጥቂት ዘረኞች ተብሎ ደግሞ የ80 ሚሊዮን ህዝብ የዴሞክራሱ ፍላጎት ሊገታ አይገባም» የሚል ሊሆን ይገባዋል፡፡ ግዜው አጭር ነው ለሚሉትም መልሳችን «ምርጫው ለሌላ ግዜ ይተላለፍ፡፡ በገዥው ፓርቲና በሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች መሃል እንዴት ምርጫውን ነጻና ፍትሃዊ ማድረግ እንደሚቻል በጋራ ጉባኤ ተቀምጠን መክረን ውሳኔ እስከምንሰጥ ምርጫው ይዘግይ» እንበላቸው፡፡

እኛ ለቆምንለት ሕዝባዊ ዓላማም ከሕዝባችን ጎን ቁመን በመሰለንና የተፈጥሮ መብታችንን ተጠቅመን በቆራጥነት እንደምንታገል ማሳዬት ይኖርብናል። ከዚህ በተረፈ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂና እውነተኛ ወዳጅነት ከፈለጉ የአገሪቱን የፖለቲካ ችግር ሙሉ በሙሉ አፍኖ የያዘውን መንግሥት ሁኔታውን እንዲለውጥ የሚችሉትን ሁሉ እንዲያድርጉ መጠየቅና ከኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት፣ የአንድነትና የዲሞክራሲ ትግል ፊት በአደናቃፊነት እንዳይቆሙ አጥብቀን ማስረዳትና በማያወላውል መልኩ ማሳወቅ ይኖርብናል። በዚህ ጠንካራ አቋማችን ለጊዜው የምእራቡ አለም መልዕክተኞች ቢጮህም፤ ምናልባትም እነሱም ጊዜያዊ ፍላጎታቸውን ስላላሟላን ሊጋፉን ቢሞክሩም፣ ውለው አድረው የሚያከብሩንን ይሆናሉ፡፡ በሃገራችን ዕውነተኛ መፍትሄ ላይ በሚችሉትና በሚፈቅዱት ልክ እንዲያተኩሩም እናደርጋቸዋለን።

ለማጠቃላልም ሁላችንም በሚቀጥለው ዓመት በመለስ-በረከት የተደገሰችልልን የማደናበርያ የመለስ-በረከት ምርጫ ዓላማዋ ምን እንደሆነ የተረዳን ይመስለናል፡፡ ለባርነት ቀንበር ህጋዊ ልባስ መስጠት ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ለዚህ «ኑና ላሞኛችሁ» የምርጫ ጥሪ መልሳችን የማያሻማ «አንዴ የተሞኘነው ይበቃል» ሊሆን ይገባዋል፡፡ መለስና-በረከት ለምርጫ ድግሳቸው ሲንደፋደፉ እኛ በእነሱ የድግስ ከበሮ ሳንደናገር ሁላችንም አቅማችን በሚፈቅድልን መጠን በሃገራችን ዴሞክራሲ እውን እንዲሆን ወደ ጀመርነው የምር ትግል ፊታችንን በጋራ እንድናዞር የግንቦት7 ንቅናቄ ይጠይቃል። የሃገራችን ሰው "ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል" እንዳለው ሁሉ እኛም ለወያኔ «የአንተ የማጭበርበሪያ ምርጫና ነጻ ምርጫ እየቅል» በማለት የሕዝብ ልጆች በአንድ ድምፅ እንንገረው!!

## በወደቁ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቹ የሚታወቀው ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ አሁንም ረሃብን አስወግዳለሁ ሲል ሌላ ዲስኩር ሰጠ

ሚሊዮኖች በየአመቱ እርዳታ በሚፈልጉባት አገር ለሃያ አመታት ስልጣንን በጉልበት ተቆጣጥሮ የቆየው ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በቅርቡ ለካድሬዎቹ ባደረገው ንግግር ረሃብን ፈጽሞ ለማጥፋት ቃል መግባቱ ታውቋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ፥ በቅርቡ መቀሌ ከሚገኙ እና "የከተማ አርበኞች" ብሎ ከሚጠራቸው ካድሬዎቹ ጋር የቪዲዮ ኮንፈረንስ ያደረገው አምባገነን፥ እያንዳንዱ አባወራ ጠግቦ የሚያድርበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች ቃል ገብቷል። ዘረኛው አምባገነን የዛሬ ሃያ አመት አዲስ አበባ እንደገባ በአምስት አመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በሙሉ በቀን ሶስቴ እንዲመገቡ እንደሚያደርግ ቃል መግባቱ እና ያንንም ቃል በሌሎች ጊዜያት መደጋገሙ ይታወሳል።

ባለፉት ሃያ አመታት ውስጥ ግን የአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ ለረሃብ የተጋለጡ ሲሆን፤ ቢያንስ አስራ አራት ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች በየአመቱ በመደበኛነት የእርዳታ ጥገኞች ናቸው። የወያኔ አገዛዝ በስራ ላይ ያዋለው ፖሊሲ የአገሪቱ የግብርና ምርት በከፍተኛ ቁጥር እንዲያድግ ማድረጉን ደጋግሞ ቢናገርም፤ ይህ እድገት በግልጽ አለመታየቱ በምሁራን እና ተመራማሪዎች ዘንድ አጠያያቂ ሆኖ ቆይቷል።

ስቴፋን ዴርኮን እና ሩት ቫርጋስ ሂል የተባሉ የእንግሊዝ ተመራማሪዎች ባለፈው ወር ባወጡት ሪፖርት፥ በኢትዮጵያ ከግብርና ጋር ተዛማች የሆኑ ምርቶች እና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ፍላጎት ሳይጨምር የግብርና ምርት አገዛዙ በሚለው ቁጥር ጨምሯል መባሉ እንቆቅልሽ መሆኑን ገልጸዋል። ከዛሬ አመት በፊት በኢትዮጵያውያን ኢኮኖሚስቶች የተፃፈ የጥናት ጽሁፍ ደግሞ፥ በወረዳ ደረጃ የሚሰሩ የልማት ሰራተኞች የሃሰት እድገት ቁጥር እየፈበረኩ እንዲያስተላልፉ በአገዛዙ ጫና እንደሚደረግባቸው አጋልጠዋል።

## የኦባማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ከሚደረገው የሰብአዊ መብት ረገጣ ላይ ትኩረቱን እንዳያዞር ጥሪ ቀረበለት

"አፍሪካ ፌይዝ ኤንድ ጀስቲስ ኔትወርክ" ወይም ኤ.ኤፍ.ጄ.ኤን የተባለ ድርጅት የኦባማ አስተዳደር ለአጭር ጊዜ ጥቅም ሲል በኢትዮጵያ ከሚካሄደው የሰብአዊ መብት ረገጣ ላይ ትኩረቱን እንዳያነሳ ጥሪ አቀረበ።

ኤ.ኤፍ.ጄ.ኤን ከአስራ ሰባት አመት በፊት የተመሰረተ እና የአሜሪካ መንግስት በአፍሪካ ላይ ያለው ፖሊሲ ሃላፊነት የተሞላው እና ፍትህና ሰላምን የሚያለመልም እንዲሆን የሚሟገት ድርጅት መሆኑን በድረ-ገጹ ላይ የሰፈረው መረጃ ያሳውቃል።

ድርጅቱ በዚህ ሳምንት ባወጣው ጽሁፍ፥ "የምርጫ ቀን የአንድን አገር ህዝብ የሚያነቃቃ ቀን ነው፤ በግንቦት 15 ቀን በኢትዮጵያ የተካሄደው ግን ተስፋና ደስታ አልነበረበትም" ብሏል። ከምርጫው በፊትና በኋላ በአገሪቱ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን ኢ-ፍትሃዊነትም ዘርዝሯል።

የነፃው አለም መሪ እና የዴሞክራሲ ተምሳሌት የሆነውችው አሜሪካ በኢትዮጵያ ኢ-ፍትሃዊነትን ከሚፈጽሙት ሃይሎች ጎን ሆና መታየቷ አሳዛኝ ነው ብሏል። ድርጅቱ፥ የአሜሪካ የአጭር ጊዜ ጥቅም ስሌት የዴሞክራሲን ጉዳይ መቅደም የለበትም ብሎ እንደሚያምን ገልጾ፤ የኦባማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን የሰብአዊ መብት ረገጣ እያየ ዝም ማለቱን እንዲያቆም አስቸኳይ ጥሪ አቅርቧል።

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

በፊታችን ቅዳሜ ሰኔ 26 በቫንኩቨር ካናዳ፤ በሳምንቱ ቅዳሜ ሐምሌ 3 በሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ የታቀዱ ዝግጅቶች እንዳሉም የኢሳት ድረ-ገጽ ላይ ከተለጠፈ ማስታወቂያ ለመረዳት ችለናል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ባለፈው ሳምንት ባወጣው ርእሰ አንቀጽ ኢትዮጵያውያን ኢሳትን እና ሌሎች ገለልተኛ መገናኛ ብዙሃንን በመደገፍ የወያኔን የመረጃ አፈና ለማኮላሸት እንዲሰሩ ጥሪ ማድረጉ ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org